ከዋጆ ረታው ሕዳር 27-2000
ሜዳ-ጋራዠ/አዲስ-አበባ

# ቃሉን ሰባበሩ!

በየመንገድ ሲቀር፤ ልቡ የታመመ
አይኑን ያጨለመ
እግሩ የደከመ፤

በአባ ላይ አባ ፤እየደራረበ
በፓልቶክ ላይ ፓልቶክ እየከማመረ
በአዲስ ሚሊኒየም ተደነባበረ
በነገር ሰከረ
ትግሉን አመረረ
ጉአዱን አማረረ
**ቃሉ፤ቃሉ ዞረ::**

አዲ-አዲስ የመጡ
ሳይገቡ የወጡ
ዕጅግ ተቀናጡ::

**የሃቂ ዕናት ሆኑ**
**የትግሉ ወራሾች**
ያልደከሙበትን መሆን ያማራቸው
ድብቅ ፍላጎቱ ባየር አወጣቸው
ቃሉን ሰባበሩ፤ያለኪዳናቸው::

## ቁረጡልኝ አለች?

«ጠቢቡ ሰለሞን
ፍርድ ሸንጎ እያለ
ባንድ ሕፃን ተጣልተው
የኔ ነች! የኔ ነች!

ለፍርድ የማይመች
ጠቢቡም ጨነቀው
በምንስ ይለየው?
ሕፃኑአም፤ሴቶቹም ቢመሳሰሉበት
ሰይፉንም አነሳ፤ፍርዱንም ለመስጠት
በሉ ዕንግዲህ ሴቶች፤ፍርዱ ደርሶአልና
ሕፃኑአን በሰይፍ፤ለሁለት እቆረጥና
ከወገቡአ በታች፤ላንቺ እሰጥሻለሁ
ከወገቡአ በላይ ላነቺኛው ሰጣለሁ
. . .ብሎ ሲነግራቸው
አንደኛዋ ክፉ፤እናተ ያልሆነችው
በል ቁረጥና-ስጠን፤እኔ እስማማለሁ
. . . ብላ ስትጨፍር
ያቺ የወለደች፤ከአብራኩአ አውጥታ
በ ሰይፍ ተቆርጦ፤ልጁአን ከመከፈል
የለም! የለም! አለች፤ጨሃትዋን ለቀቀች
ለጄን ለሁለት ከሚከፍሉአት
ይህቺ ሴተዮ ወስዳ ታሳድጋት
በማለት ነበር፤ልጁአን ከመከፈል
. . . ያዳነችአት ከሞት
ጠቢቡም  ሰለሞን ነገሩን ተረድቶት
እንዲህ አለ ፍርዱን
ህጻን እንዲታርድ  ጭፈራ ያበዛሺው!
ያንቺ ልጅ  አይደለም አንግዲህ ዕረፊው
ዕውነተኛ እናት ከምር ያስታውቃል
ልጅቱ ያንቺ ናት!
ፅናትሽ ይገርማል፤እንቺ ብሎ ሰጥቶ አሰነባበታት»

<u>በቅዱስ መፅሀፍ ላይ</u>
<u>የነበረ የጥነቱ ምሳሌ</u>
<u>በጠቀመን ነበር፤እነሆ ለዛሬ</u>
<u>ራስ ወደድንና</u>
<u>ያን ሁሉ መስዋዕት፤ልናስቀረው መና::</u>

**ለመክፈል ተነሳን**
**ለመቁረጥ ደፈርን**
**ልብ እየተነሳን**
**30 ዓመት በፊት. . .**
**. . . ብተና ጀምረን**
**. . . ያውም በጉርምስናችን**
**«መለስ» በለን መጣን**
**ዘንድሮም ብተና ከነማረጋችን።**

**እንፈር!!!**

**ደሕና ቆዩ ዕድምተኞቼ**